# የተጠቃሚ በባቡር ወደ SEA Airport መሄጃ መመሪያ

ወደ SEA Airport መጓዝ በመጀመሪያ ተስፋ አስቆራጭ ቢመስልም እንኳ ተርሚናሉ ከሁለት እስከ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ በቀላሉ ወደሚፈልጉበት ቦታ ለመሄድ በሚያስችልዎ ደረጃ አጭር ነው! ከዚህ በታች የቀረበው ወደ SEA Airport እንዴት በተርሚናል የባቡር ሲስተም መሄድ እንደሚችሉ የተመለከተ መመሪያ ነው።

## የጉዞ ፍንጮች:

- በጉዞ ወቅት በመግቢያዎ ላይ ደረጃ በደረጃ የሚከተሏቸውን መመሪያዎች ለማግኘት በድረ ገጹ ላይ የሚገኘውን የሀሳብ መለዋወጫ ካርታ ይጠቀሙ።
- ወይም አሁን ስላሉበት ቦታ የሚያሳይ የሀሳብ መለዋወጫ ካርታ የሚይዘው በiOS እና አንድሮይድ ስልኮች ላይ የሚገኘውን ነጻ የFlySEA መተግበሪያ ያውርዱ።

## ቀላል መድረሻዎች

በSEA Airport የሚገኙ ሁሉም አየር መንገዶች እርስ በርሳቸው የተገናኙና የደህንነት ፍተሻ ቦታዎቹን ካለፉ በኋላ በቀላሉ ለመድረስ የሚያስችሉ ናቸው። ወደ SEA ሲደርሱ በድጋሚ በTSA ማጣሪያ ማለፍ የማይጠበቅብዎ ሆኖ በቀጥታ ወደ ቀጣዩ በረራዎ መሄድ ይችላሉ። የሚመጡትና የሚሄዱት በተመሳሳይ አየር መንገድ ከሆነ መግቢያ በርዎችዎ በንጽጽር የተጠጋጉ መሆን አለባቸው። ስለ አየር መንገዶች እና ስለመግቢያ በሮቻቸው ከታች ዝርዝሩን።

***ቦታዎች ሊቀየሩ ስለሚችሉ በረራዎን እና የመግቢያ በሩን ከመሳፈሪያ ይለፍዎ፣ ከተርሚናሉ ስክሪኖች ወይም ከFlySEA መተግበሪያ ላይ ደጋግመው ማረጋገጥዎን አይርሱ።***

## የአየር መንገድ ቦታዎች በበር:

- **ኤር ሊንገስ/Aer Lingus:** የA በሮች
- **ኤሮ ሜክሲኮ/AeroMexico:** የS በሮች
- **ኤየር ካናዳ/Air Canada:** የA በሮች
- **ኤየር ፍራንስ/Air France:** የS በሮች
- **አላስካ አየር መንገድ/Alaska Airlines:** የC, D, እና N በሮች
- **አሜሪካን ኤር ላይንስ/American Airlines:** የD በሮች
- **ANA:** የS በሮች
- **ኤዢያን ኤር ላይንስ/Asiana Airlines:** የS በሮች
- **ሄይናን ኤየር ላይንስ/Hainan Airlines:** የS በሮች
- **ሀዋያን ኤየር ላይንስ/Hawaiian Airlines:** የS በሮች
- **አይላንደር/Icelandair:** የS በሮች
- **ጃፓን ኤየር ላይንስ/Japan Airlines:** የA በሮች
- **ጄት ብሉ ኤየር ዌይስ/JetBlue Airways:** የA በሮች
- **ኮርያን ኤየር/Korean Air:** የS በሮች
- **ሉፍታንዛ/Lufthansa:** የS በሮች
- **ቃታር ኤየር ዌይስ/Qatar Airways:** የS በሮች
- **ሲንጋፖር ኤየር ላይንስ/Singapore Airlines:** የS በሮች
- **ሳውዝ ዌስት ኤየር ላየይንስ/Southwest Airlines:** የB በሮች

| | |
|---|---|
| <ul><li>**ብሪቲሽ ኤር ዌይስ/British Airways:** የS በሮች</li><li>**ካቴ ፓሲፊክ/Cathay Pacific:** የS በሮች</li><li>**ኮንዶር/Condor:** የS በሮች</li><li>**ዴልታ ኤር ላይንስ/Delta Air Lines:** የS እና A በሮች</li><li>**ኢሜሬትስ/Emirates:** የS በሮች</li><li>**ኢቪኤ ኤየር/EVA Air:** የS በሮች</li><li>**ፍሮንቲር ኤየር ላይንስ/Frontier Airlines:** የB በሮች</li></ul> | <ul><li>**ስፒሪት ኤየር ላይንስ/Spirit Airlines:** የመሳፈሪያ ይለፈዎን ይመልከቱ</li><li>**ሰን ካንትሪ ኤየር ላይንስ/Sun Country Airlines:** የመሳፈሪያ ይለፈዎን ይመልከቱ</li><li>**ዩናይትድ ኤየር ላይንስ/United Airlines:** የA በሮች</li><li>**ቨርጂን ኤየር ላይንስ/Virgin Atlantic:** የS በሮች</li><li>**ቮላሪስ/Volaris:** የS በሮች</li></ul> |

## የተርሚናል ጠቅላላ ምልከታ

ሲያትል - ታኮማ አለም አቀፍ አየር መንገድ/Seattle-Tacoma International Airport (SEA) አራት የህዝብ መተላለፊያዎችና ሁለት ሳተላይቶች ያሉት አንድ ተርሚናል አለው። እያንዳንዱን በር በሰሜን እና የደቡብ የባቡር ሲስተሞች ማግኘት ይቻላል። ወዴት እንደሚሄዱ ለማወቅ ምልክቱን ይመልከቱ፣ አረንጓዴ ሸሚዝ ለባሽ መንገድ መሪውን ይጠይቁ ወይም የባቡር መሳፈሪያ መመሪያዎችን (በተለያዩ ቋንቋዎች) ይቆጣጠሩ።

## እንዴት መድረስ እችላለሁ

ለተሳፋሪዎቻችን ወዴት መሄድ እንደሚፈልጉ ድጋፍ በመስጠት የሚረዱ በስምንት ቋንቋዎች የተዘጋጁ የባቡር የምልክት ማሳያዎች አሉ፡ አረቢኛ፣ ቻይኒኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ጃፓኒኛ፣ ኮርያኛ፣ ራሺያኛ፣ ስፓኒሽ እና የቬትናም ቋንቋ! ምልክት ማሳያዎቹ የትኛው ማቆሚያ ላይ እንዳሉ፣ ቀጣዩ ማቆሚያ የት እንደሆነ የተመለከተ ማስታወቂያና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጣሉ።

### *የተርሚናል መንኩራኩር/ Yellow Loop:*

Yellow Loop ተብሎ የሚጠራ የተርሚናል መንኩራኩር አለ።

- ይህ አገናኝ ወደ እንዳንዱ ባቡር ጣቢያ የ **S, B, እና A በሮች እና ወደ N, C, እና D** በሮች ይወስድዎታል!
- እነዚህ ጣቢያዎች በ **D እና A በሮች የሚገኙ ሲሆን** አስፈላጊ ከሆነ በሁለት ጣቢያዎች መካከል መንኩራኩር መጠቀምም ይችላሉ። ከዚህ በመነሳት ከአንድ የባቡር ሉፕ ወደ ሌላ በቀላሉ መሸጋገር ይቻላል።

### *South Train Loop/Blue Loop:*

የA, B, እና S በሮች ሁሉም በተርሚናሉ ደቡባዊ ጫፍ። ሁሉም አለም አቀፍ አየር መንገዶች በሚባል ደረጃ በS በሮች ወይም በተርሚናሉ ደቡባዊ ጫፍ በኩል ይሰራሉ።

- **የA ጣቢያ** ከበር A3 ጀምሮ ወደ ታች እስከ ማሳለጫ ባንኩ ድረስ ይሄዳል።
- **የB ጣቢያ** ከህዝብ መተላለፊያው ጀምሮ ወደ ታች ከበር B20/21 እስከ ማሳለጫዎቹ ይሄዳል።
- **የS ጣቢያ** ከሁሉም የS በሮች የህዝብ መተላለፊያ በታች ይገኛል።

*North Train Loop/Green Loop:*

የD, N, እና C በሮች ሁሉም በተርሚናሉ ሰሜናዊ ክፍል መጨረሻ ላይ ይገኛሉ። ይህ ሉፕ በC, D, እና N በሮች ለሚሰሩ ለአብዛኞቹ የአላስካ አየር መንገድ/ Alaska Airline በረራዎች ያገለግላል።

- **የD በሮች ጣቢያ** ከበር D2 ጀምሮ እስከ ማሳለጫዎቹ በታች የሚሰራ ሲሆን የ C ጣቢያ በማሳለጫዎቹ ወደ ታች እስከ በር C11 ይሄዳል።
- **የN በሮች ጣቢያ** ከሁሉም የN በሮች ከህዝብ መተላለፊያ ደረጃ በታች ይገኛል።
- **የC በሮች ጣቢያ** በቅርቡ እድሳት የተደረገለት ሲሆን አዲስ Cascadia ተብሎ የሚጠራ የመስታወት አርት ባህሪያት የተሰሩለት ከመሆኑም በተጨማሪ በእያንዳንዱ ጣቢያ ላይ ሌሎች አርቶች ተሰርተዋል።

**ተርሚናሉን ለማግኘት እንዲረዳዎ የ<u>FlySEA መተግበሪያን</u> ያውርዱ!**

******